# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውም ውሳኔ የማረም የሰበር ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት የተመለከተ በመሆኑ፤

የዚህ ሕገ-መንግስታዊ ሥልጣን ዋና ዓላማ ፍርድ ቤቶች እና በሕግ የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸዉ ሌሎች አካላት በሚሰጡት የመጨረሻ ውሳኔ የሚፈጽሙትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በማረም በሀገሪቱ ዉስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎም ሥርዓት ማስፈን፣ ትክክለኛ የሕግ አተገባበር እንዲኖር እንዲሁም የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ማድረግ በመሆኑ፤

የሰበር የዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓት ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች እና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ አንቀጽ 1234/2013 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ሰበር ችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ክርክር አመራር ሥርዓት በተመለከተ መመሪያ የማውጣት ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ አንቀጽ 1234/2013 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይህንን የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 የተጠቀሱ ቃላቶች ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ብቻ በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ማለት ነው፡፡
2. **"ፍርድ ቤት"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 ሥር በተሰጠው ትርጓሜ መሰረት የመጨረሻ ፍርድ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔን የመስጠት ስልጣን የተሰጣቸውን የክልል ፍርድ ቤቶችን፣የከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች፣ አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች እና በሌሎች ሕጎች መሰረት የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት እና ተቋማት ናቸዉ፤
3. **"የሰበር አጣሪ ችሎት"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሶስት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የሚሰየሙበት ማለት ነው፡፡
4. **"ሰበር ችሎት"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከአምስት ያላነሱ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የሚሰየሙበት ማለት ነው፡፡
5. **"የሰበር አቤቱታ"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 27 መሰረት የሚቀርብ ማመልከቻ ማለት ነው፡፡

**3. የጾታ አገላለጽ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የሰበር አቤቱታ ማመልከቻ ይዘትና የጊዜ ገደብ

**4. የሰበር አቤቱታ ይዘት**

1. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሰበር አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ሲቀርብ የአቤቱታውን መግቢያ ሳይጨምር በሶስት (3) ገጽ ብቻ ተጽፎ የተዘጋጀ ሆኖ የጽሑፉ የመስመር ክፍተት በአንድ ነጥብ አምስት (1.5)፣ የዙሪያው ህዳግ አንድ (1) ኢንች፣ የፊደሎቹ የቃላት መጠን ወይም ፎንት አስራ ሁለት (12) ሆኖ በፓወር ግዕዝ ቅርጽ ወይም ለፓወር ግዕዝ ከተቀመጡት ዝርዝር መስፈርቶች ጋር ተመሳሳይነት ባላቸዉ አኳኋን መዘጋጀት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አቤቱታ አቅራቢው ከሰበር አቤቱታዉ ይዘት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው ብሎ የሚያምንበትን ሌሎች ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ከአቤቱታው ጋር በአባሪ ማያያዝ ይችላል። ሆኖም ችሎቱ በአቤቱታው የቀረበው በቂ ነው ብሎ ካመነ አባሪውን መመልከት ሳያስፈልገው በቀረበዉ አቤቱታ ላይ ብቻ ተመሥርቶ ተገቢዉን ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ የሰበር አቤቱታ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች መያዝ አለበት፡፡

   ሀ. የአመልካችና የተጠሪ ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

   ለ. የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት እና መዝገብ ቁጥር

   ሐ. አግባብነት ያለውን የአቤቱታውን መነሻ ነጥቦች በአጭሩ፣

   መ. አመልካቹ ለአቤቱታው መሰረት ያደረገው ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ስለሚለው መሰረታዊ የሕግ ስህተት እና በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 /ሀ/ - /ሸ/ እና አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከተዘረዘሩት አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ሊያሰኝ የሚያስችል ምክንያት በአጭሩ፣

   መ. ከሰበር ችሎቱ የሚጠየቀዉ ዳኝነት

4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ/ - /መ/ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሰበር አቤቱታው የቀረበበትን ውሣኔ እና የበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅጂዎችን እንዲሁም ዉሳኔዉ ከፌዴራል የሥራ ቋንቋ ዉጪ በሆነ ቋንቋ የተሰጠ ከሆነ ትርጉሙን አመልካቹ ከአቤቱታው ጋር አባሪ አድርጎ ማቅረብ ያለበት ሲሆን አቤቱታዉ ያስቀርባል ከተባለ ዉሳኔዉን እና ዋናዉን ቅጂ ከእነትርጉሙ ለተጠሪ እንዲደርስ በበቂ ቅጂ ማቅረብ አለበት።

5. ማንኛውም የሰበር አቤቱታ ስለ እውነተኛነቱ በአመልካቹ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ ወይም በጠበቃው አማካኝነት ተረጋግጦ የተፈረመ መሆን ይኖርበታል፡፡

6. ለፍርድ ቤቱ የሚቀርብ ማንኛውም የሰበር አቤቱታ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ቅጽ መሰረት መቅረብ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 6 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት የሰበር አቤቱታው ተዘጋጅቶ ለፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ወይም ለኢ-ፋይሊንግ ማዕከል በሰነድ መልክ እና በሶፍት ኮፒ ጭምር መቅረብ አለበት።
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ሥር ከተደነገገዉ በተቃራኒ የሰበር አቤቱታው መዝገብ ተከፍቶ ለችሎቱ ከቀረበ ችሎቱ አቤቱታው ተሻሽሎ እንዲቀርብ ወይም ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

**5. የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ያልቀረበ የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜዉ ያለፈበት ማመልከቻ የቀረበለት የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር አመልካቹ በአሥር ቀናት ዉስጥ የሰበር አቤቱታ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችል መሆኑን በመግለጽ አቤቱታዉን ይመልስለታል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም አመልካቹ የሰበር አቤቱታውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በቂና አሳማኝ በሆነ ምክንያት ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ በማስረጃ ወይም በቃለ-መሐላ በማስደገፍ ሰበር አቤቱታውን እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት አቤቱታዉን ለሰበር አጣሪ ችሎት ማቅረብ ይችላል፡፡
4. የሰበር አጣሪ ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የቀረበለትን አቤቱታ ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተጠሪን አስተያየት መስማት ይችላል፡፡

5. የሰበር አጣሪ ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በአመልካች የቀረበው ምክንያት አሳማኝ መሆኑን ከተረዳ አመልካቹ የሰበር አቤቱታውን ችሎቱ በሚሰጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ለፍርድ ቤቱ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

6. የሰበር አጣሪ ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በአመልካች የቀረበውን ምክንያት ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በጽሑፍ በማስፈር አቤቱታውን ውድቅ አድርጎ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የሰበር አቤቱታ አቀራረብ እና የክርክር አመራር

### 6. የሰበር አቤቱታ ስለሚቀርብበት ስነ-ሥርዓት

1. የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎቱ የሚቀርበውና የሚሰማው በአዋጁ አንቀጽ 28 በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታው አስቀድሞ የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉ የቀረበበት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከተመለከቱት ምክንያቶች አንጻር በሰበር ችሎት መታየት አለበት ብሎ ሲወስን ብቻ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሰረት የሰበር አጣሪ ችሎቱ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ከመወሰኑ በፊት አቤቱታው የሚሰማበትን ቀን በመወሰን አመልካቹን መስማት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሰበር አጣሪ ችሎቱ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ለዉሳኔዉ ምክንያት የሆኑትን ነጥቦች በጽሑፍ ማስፈር አለበት፡፡

### 7. የሰበር ችሎት የክርክር አመራር

**1.** የሰበር ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከሰበር አጣሪ ችሎቱ የተመራለትን የሰበር መዝገብ በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከመረመረ

በኃላ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለመኖሩን ከተረዳ ምክንያቱን በጽሑፍ ማስፈር አቤቱታውን ውድቅ አድርጎ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ዉሳኔ ከመስጠቱ በፊት በቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ላይ ተጨማሪ ማጣራት ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ አቤቱታው የሚሰማበትን ቀን በመወሰንና አመልካቹን በመጥራት ሊሰማ ይችላል፡፡

3. በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሰረት የሰበር ችሎቱ ከሰበር አጣሪ ችሎቱ የተመራለትን መዝገብ መርምሮ ለሰበር ያስቀርባል ብሎ ከወሰነ ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 አንጻር የሰበር ክርክሩን ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ በጽሁፍ መልሱን እንዲያቀርብ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ከመጥሪያ ጋር እንዲደርሰው ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አቤቱታዉ የቀረበበት የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተሰጠዉ ከፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ ዉጪ በሆነ ቋንቋ ከሆነ ዉሳኔዉን እና የትርጉሙን ቅጂ ፍርድ ቤቱ ለተጠሪ ከመጥሪያዉ ጋር እንዲደርሰዉ ትዕዛዝ ይለሰጣል።

5. የሰበር ችሎቱ በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት እና በዚህ መመሪያ መሰረት ተከራካሪዎች መልስ እና የመልስ መልስ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበው ከተቀባበሉ በኋላ ተከራካሪዎችን መስማት ካላስፈለገው በስተቀር በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ግን ሰበር ችሎቱ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ፣ ከቀረበው የተጠሪ መልስ እና የመልስ መልስ ጋር አጣምሮ ከመረመረ በኋላ ግራ ቀኙን መስማት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ክርክሩ የሚሰማበትን ቀን ወስኖ የቀጠሮ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰበር ችሎቱ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር ከመረመረ በኃላ አስቀድሞ የያዘዉን ጭብጥ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘዉ በተለወጠዉ ወይም በተሻሻለዉ ጭብጥ ላይ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር መስማት አለበት።

## 8. መልስና የመልስ መልስ አቀራረብ

1. በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት መጥሪያ ደርሶት መልሱን እንዲያቀርብ በሰበር ችሎቱ ትእዛዝ የተሰጠው ተጠሪ በሰበር ችሎቱ በተወሰነው ቀን መልሱን ይዞ መቅረብ አለበት፡፡

2. ተጠሪ የሚያቀርበው መልስ የሰበር መዝገቡን በመጥቀስ እና እንደ አግባብነታቸዉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 3 (ሀ፣ ለ)፣ 5 እና 6 መሰረት በማድረግ በሰበር አቤቱታዉ የተነሳውን መሰረታዊ የሕግ ክርክር እና በሰበር ችሎቱ በተያዘው ጭብጥ ላይ ተወስኖ በአጭሩ ተዘጋጅቶ በሰነድ መልክ እና በሶፍት ኮፒ ለሰበር ችሎቱ መቅረብ አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ከተደነገገዉ በተቃራኒ የተጠሪ መልስ ለሰበር ችሎቱ ከቀረበ ችሎቱ መልሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ወይም ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ በአመልካች ከቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት እና በሰበር ችሎቱ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸዉ ሌሎች ተጨማሪ ማብራሪያዎች አለኝ ብሎ ካመነ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል።

5. ተጠሪ በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካለው በመልሱ ዉስጥ አካቶ ማቅረብ አለበት ሲሆን የሰበር ክርክርን አስመልክቶ በተጠሪ የሚቀርቡት የሰበር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ምክንያቶች፡-

    ሀ. የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ፤

    ለ. በችሎቱ ወይም በሰበር ችሎቱ አስቀድሞ ታይቶ የተዘጋ ወይም ውሳኔ ያገኘ ስለመሆኑ፤ ወይም

ሐ. የቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች አስቀድሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግስት ትርጉም የተሰጠበት ስለመሆኑ፣

መ. የቀረበው የሰበር አቤቱታ የመጨረሻ ፍርድ ያልተሰጠበት ስለመሆኑ፣

ሠ. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ለሰበር ከቀረበ በኋለ በእርቅ ያለቀ ስለመሆኑ፣

ረ. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ለሰበር ከቀረበ በኋላ የክርክሩ ምክንያት ተቋርጧል የሚል ወይም ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸዉ መቃወሚያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6. የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መሰረት በማድረግ በተያዘዉ መዝገብ ላይ በማንኛውም የሰበር ክርክር ደረጃ ላይ የሚቀርብ የተጠሪ የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረዉም፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት አመልካቹ የሰበር ችሎቱን መጥሪያ ባለማድረሱ ተጠሪ ያልቀረበ እንደሆነ ወይም አመልካች መጥሪያዉን ዘግይቶ በማድረሱ ምክንያት ተጠሪ መልሱን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ ያላገኘ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ የሰበር ችሎቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ብይን በመስጠት ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

8. አመልካች ከተጠሪ ለቀረበው መልስ በሰበር ችሎቱ በሚወሰነው ቀን የመልስ መልስ ማቅረብ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በአመልካች የሚቀርበዉ የመልስ መልስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ፣ 2 ፣ 5 እና 6 ሥር የተደነገገዉን መሰረት ያደረገ ሆኖ በተጠሪ በቀረበዉ መልስ ላይ ብቻ የተወሰነ እና አዲስ ክርክር ያልተካተተበት መሆን አለበት፡፡

9. የሰበር ችሎቱ ከቀረበለት የሰበር አቤቱታ ወይም ከያዘው ጭብጥ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ወይም ያላቸው የሰበር አቤቱታ መዝገቦች ካሉ ወይም መኖራቸውን ከተረዳ

በባለጉዳዮች አመልካችነት ወይም በራሱ አነሳሽነት መዝገቦቹ ተጣምረው እንዲታዩ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

10.የሰበር ችሎቱ እንደ አስፈላጊነቱ መልስ እና የመልስ መልስ የማቀባበል ስራን በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር፣ በሰበር ችሎቱ ረዳት ዳኛ ወይም በኢ-ፋይሊንግ ማዕከል በኩል እንዲከናወን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**9. የሰበር ችሎት ሥልጣን**

1. የሰበር ችሎቱ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔን የማጽናት፣ የማሻሻል፣ የመለወጥ ወይም ሙሉ በሙሉ የመሻር ስልጣን አለው፡፡ በዚህ መሰረት የሰበር ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ፡-
   ሀ. አቤቱታ በቀረበበት የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለመኖሩን ከተረዳ ውሳኔን በማጽናት ይወስናል፡፡
   ለ. አቤቱታ በቀረበበት የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖሩን ከተረዳ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔን በማሻሻል፣ በመለወጥ ወይም በመሻር ይወስናል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ሥር የተደረነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በሰበር ችሎቱ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ካልሆነ፣ ትክክለኛ ጭብጥ ሳይይዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ በመያዝ የሰጠዉን ዉሳኔ ወይም የማስረጃ አቀባበል እና የምዘና መርህን በመጣስ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ሆኖ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት ማስረጃ በመስማትና እና በመመዘን ፍሬ ነገርን ማረጋገጥ የግድ የሚል ካልሆነ በስተቀር ሰበር ችሎቱ መዝገቡን ወደ ሥር ፍርድ ቤት አይመልስም።

## 10. የአመልካች እና የተጠሪ አለመቅረብ የሚያስከትለዉ ዉጤት

1. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7 ሥር የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የአመልካችና የተጠሪ አለመቅረብ የሚያስከትለው ውጤት በተመለከተ እንደ አስፈላጊነታቸዉ አግባብነት ያላቸው የፍትሐ ብሔር ስነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡
2. የሰበር አጣሪ ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አመልካችን ለመስማት በያዘው ቀጠሮ አመልካቹ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተገቢውን ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን ይዘጋል፡፡
3. የሰበር ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አመልካችን ለመስማት በያዘው ቀጠሮ አመልካቹ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተገቢውን ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን ይዘጋል፡፡
4. የሰበር ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ በያዘው ቀጠሮ ተጠሪው መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ መልሱን በጽሁፍ የማቅረብ መብቱ ታልፎ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ እና ትዕዛዝ ይሰጣል።
5. የሰበር ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ግራ ቀኙን ለመስማት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አመልካቹ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተጠሪን ብቻ በመስማት በሰበር አቤቱታው ክርክር ላይ ተገቢውን ውሳኔና ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
6. የሰበር ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ግራ ቀኙን ለመስማት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጠሪ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ አመልካችን ብቻ በመስማት በሰበር አቤቱታ ክርክር ላይ ተገቢውን ውሳኔና ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

7. የሰበር ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ግራ ቀኙን ለመስማት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ግራ ቀኙ ወገኖች ካልቀረቡ የተከራካሪ ወገኖችን የጽሁፍ ክርክር በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ እና ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
8. የሰበር ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት ግራ ቀኙን ለመስማት በሰጠዉ ትዕዛዝ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም አንዳቸዉ ሳይቀርቡ የቀረ እንደሆነ ችሎቱ ተገቢ ነዉ ብሎ ያመነበትን ዉሳኔ ወይም ትዕዛዝ ይሰጣል።
9. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ የሰበር ችሎቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ተከራካሪ ወገኖች በአካል መቅረብ ሳያስፈልጋቸዉ በቪዲዮ ኮንፍረንስ፣ በኢ-ፋይሊንግ ወይም ሌላ አመቺ በሆነ መንገድ እንዲሰሙ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።

## 11. በወንጀል ጉዳዮች ላይ የሰበር አመልካችና ተጠሪ ስለመቅረብ

1. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 10 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ጉዳይ ተጠሪው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተወስኖበት በማረሚያ ቤት ሆኖ የእስራት ቅጣቱን እየፈጸመ የሚገኝ ከሆነ ወይም በተጠረጠረበት ወይም በተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት ያልተፈቀደለት በመሆኑ በማረሚያ ቤት ሆኖ ጉዳዩን እየተከታተለ ከሆነ ዓቃቤ ሕግ የፍርድ ቤቱን መጥሪያ ከሰበር አቤቱታው ጋር ለተጠሪ ማድረስ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ዓቃቤ ሕግ ለተጠሪው መጥሪያውን ሳያደርስ የቀረ እንደሆነ ወይም በቂ በሆነ ጊዜ ዉስጥ ሳያደርስ በመቅረቱ ምክንያት ተጠሪ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ወይም መልሱን ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ የሰበር ችሎቱ የነገሩን ሁኔታ በመመርመር ተገቢ ነዉ ብሎ ያመነበትን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

3. ተጠሪ በነጻ ተለቆ ወይም ቅጣቱን ፈጽሞ ወይም ቅጣቱ ተገድቦለት ወይም በዋስትና ተለቆ በውጪ ሆኖ ጉዳዩን እየተከታተለ ከሆነ ዓቃቤ ሕግ መጥሪያው በፖሊስ በኩል ለተጠሪ እንዲደርሰዉ የሰበር ችሎቱን መጠየቅ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ዓቃቤ ሕግ ወይም መጥሪያዉን እንዲያደርስ የታዘዘዉ ፖሊስ የተጠሪን አድራሻ ማግኘት ያልቻለ እንደሆነ ዓቃቤ ሕግ ይህንኑ በማስረጃ አስደግፎ ለሰበር ችሎቱ መጥሪያውን ይመልሳል፡፡ የሰበር ችሎቱም የአቃቤ ሕግን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ሌሎች የመጥሪያ አደራረስ ስልቶችን ሊከተል ወይም ሌላ ተገቢ ነዉ ብሎ ያመነበትን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. በወንጀል ጉዳይ የሰበር አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው በጠበቃ ሳይወከል ከማረሚያ ቤት ከሆነ ማረሚያ ቤቱ ወዲያውኑ አቤቱታውን ለሰበር ችሎቱ ይልካል፡፡ አቤቱታዉ የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አመልካችን ለመስማት በተቀጠረዉ ቀን ማረሚያ ቤቱ አመልካችን እንዲቀያርብ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

6. የሰበር አመልካች ከማረሚያ ቤት ሆኖ ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ የሰበር ችሎቱ በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ለሰበር ያስቀርባል ብሎ ከወሰነ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ከመጥሪያ ጋር ለዓቃቤ ሕግ እንዲደርሰው ትዕዛዝ ይሰጣል።

7. የሰበር ችሎቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተመራለትን መዝገብ በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት መርምሮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር በተደነገገዉ መሰረት አመልካቹን ለመስማት ትዕዛዝ የሰጠ እንደሆነ አመልካችን ለመስማት በተቀጠረዉ ቀን ማረሚያ ቤቱ አመልካችን እንዲቀያርብ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

8. የሰበር ችሎት ከማረሚያ ቤት ሆኖ ጉዳዩን እየተከታተለ ያለዉን የሰበር አመልካች ወይም ተጠሪን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 ወይም 6 መሰረት ለመስማት ትዕዛዝ የሰጠ እንደሆነ በተቀጠረዉ ቀን ማረሚያ ቤቱ አመልካችን ወይም ተጠሪን እንዲቀያርብ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

9. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ የሰበር ችሎቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ እንደ ነገሩ ሁኔታ የሰበር አመልካች ወይም ተጠሪ በማረሚያ ቤት ሆኖ ጉዳዩን እየተከታተለ ከሆነ በአካል መቅረብ ሳያስፈልገዉ ከማረሚያ ቤት፣ በቪዲዮ ኮንፍረንስ፣ በኢ-ፋይሊንግ ወይም ሌላ አመቺ በሆነ መንገድ እንዲሰማ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።

**12. በሰበር ክርክር ተሳታፊ ስለመሆን**

1. በሥር በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች ተካፋይ የነበረ እና በሰበር ክርክር ተሳታፊ ያልተደረገ ሰዉ በሰበር ችሎቱ አነሳሽነት ወይም በአቤት ባዩ አመልካችነት በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የሰበር ችሎቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።
2. በሥር ፍርድ ቤቶች ተከራካሪ ያልነበረ ማንኛዉም ሰዉ በሰበር ክርክር ተሳታፊ ለመሆን የሚያቀርበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም።

**13. ስለ ፍርድ ቤት አጋር (አማይከስ ኩሬ)**

1. **"የፍርድ ቤት አጋር"** ማለት በሰበር ችሎቱ በቀረበው ጉዳይ ላይ ምንም አይነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ምንም አይነት የግል ጥቅም የሌለው/ላቸው ሆነው በሰበር ችሎቱ ትዕዛዝ መሰረት ለሰበር ችሎቱ በቀረበዉ ጉዳይ፣ በሰበር ችሎቱ በተያዘዉ ጭብጥ ላይ ወይም ሳይንሳዊ አስተያየት እንዲቀርብለት በሰበር ችሎቱ በተለየዉ ርዕስ ላይ ግልጽ ሳይንሳዊ ሂደትን በመከተል ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙያዊ አስተያየት እና ትንታኔ የሚሰጥ/ጡ ባለሙያ/ዎች፣ የሙያ ማህበራት ወይም ሌሎች መሰል ተቋማት ማለት ነው፡፡

2. የሰበር ችሎቱ በቀረበለት የሰበር አቤቱታ እና በያዘው ጭብጥ ላይ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑት የፍርድ ቤት አጋር ወይም አጋሮችን መስማት ተገቢ መሆኑን ካመነ ለተያዘው ጭብጥ ተገቢነት ያለውን/ያላቸዉን አጋር/ አጋሮች በመለየት እና የሚሰማበትን/ሙበትን ዝርዝር ሁኔታ በመወሰን አስተያየት ሊቀበል ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚጠራው/ሩት የፍርድ ቤት አጋር/ አጋሮች የሚሰጠው/ጡት አስተያየት በጽሁፍ ሆኖ እንደነገሩ ሁኔታ በግልጽ ችሎትም ቀርቦ በቃል እንዲሰሙ የሰበር ችሎቱ ሊጋብዝ ይችላል፡፡

## 14. ከሰባት ያላነሱ ዳኞች ስለሚሰየሙበት የሰበር ችሎት

1. የሰበር ችሎት በራሱ አነሳሽነት ወይም በባለጉዳዮች አመልካችነት የሰበር አቤቱታዉ ከሰበት ያላነሱ ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በቂና አሳማኝ ምክንያቶችን በመተንተን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ማቅረብ ይችላል፡፡ ፕሬዚዳንቱም ከሰበር ችሎቱ የቀረበዉን ጥያቄ መሰረት በማድረግ በአዋጁ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት ጉዳዩ ከሰባት ያላነሱ ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት እንዲታይ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለሰበር ችሎት የቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ከሰባት ያላነሱ ዳኞች በሚሰየሙበት ሰበር ችሎት ቀርቦ የሚታየዉ አስቀድሞ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በተሰጠባቸዉ የሰበር ችሎት ዉሳኔዎች መካከል ተቃርኖ መኖሩ ሲረጋገጥ ወይም አስቀድሞ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በተለያዩ ምክንያቶች ማሻሻል ወይም መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነዉ፡፡

## 15. የሰበር ችሎት የፍርድ ውሳኔ አሰጣጥ እና ይዘት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና 8 መሰረት የግራ ቀኙ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ የሰበር ችሎቱ ፍርድና ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2. በሰበር ችሎቱ በተሰየሙ ዳኞች መካከል የሃሳብ ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ የችሎቱ አብላጫ ድምጽ የሰበር ችሎቱ ውሳኔ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የልዩነት ወይም የመስማሚያ ሃሳብ ያለው ወይም ያላቸው ዳኛ ወይም ዳኞች በተናጠል ወይም በጋራ የልዩነት ሃሳቡን ወይም ሃሳባቸውን ወዲያውኑ ከሰበር ችሎቱ ውሳኔ ጋር ማያያዝ አለባቸው፡፡

3. የሰበር ችሎቱ ፍርድና ውሳኔ የሚከተሉትን ዝርዝር ነገሮች መያዝ አለበት፡፡

   ሀ. የሰበር መዝገብ ቁጥር፣

   ለ. የሰበር ችሎቱ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፣

   ሐ. በሰበር ችሎቱ የተሰየሙ ዳኞች ስም ዝርዝር፣

   መ. የአመልካች እና የተጠሪ ሙሉ ስም፣

   ሠ. ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የመጨረሻ ውሳኔ መዝገብ ቁጥር፣ ውሳኔ የተሰጠበት ቀን እና ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት ወይም አካል፣

   ረ. በተከራካሪ ወገኖች መካከል መሰረታዊ የሕግ ስህተትን አስመልክቶ ስለቀረበው ክርክር በአጭሩ እና በሰበር ችሎቱ የተያዘው ጭብጥ፣

   ሰ. የሰበር ችሎቱ የፍርድ ውሳኔ የተመሰረተበት የሕግ ድንጋጌ/ዎች፣ አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ/ዎች ከእነ አግባብነቱ/ታቸው እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ምንጮች፣

   ሸ. የሰበር ችሎቱ ትንታኔና የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው ብይን/ኖች እና ትዕዛዝ/ዞች፣

4. የሰበር ችሎቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት በሚሰጠዉ ፍርድና ወሳኔ ዉስጥ በቂና ተገቢ ትንታኔ ካሰፈረ በኋላ በፍርዱ መደምደሚያ ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶ ከሆነ የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በአጭሩ ይገልጻል፤ የፍርዱን ዉጤት የሚያመላክት ዉሳኔ እና አግባብነት ያለዉን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**16. ፍርድ ለመቃወም ስለሚቀርብ አቤቱታ**

1. በሰበር ችሎት በነበረዉ ክርክር ተካፋይ ሳልሆን መብቴን ወይም ጥቅሜን የሚነካ ዉሳኔ ተሰጠብኝ በሚል የሰበር የፍርድ ዉሳኔ በመቃወም የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገዉ ቢኖርም መቃወሚያ የቀረበበት የፍርድ ዉሳኔ በሰበር ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በሆነ ጊዜ፡-
    ሀ. የሰበር መቃወሚያ አመልካቹ በሥር ፍርድ ቤት የክርክሩ ተካፋይ ያልነበረ ከሆነ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት የተመለከተዉ ፍርድ ቤት የመቃወም አመልካቹን መቃወሚያ ተቀብሎ እንዲያከራክር የሰበር ችሎት በመዝገቡ ላይ ትእዛዝ በመስጠት ሊመራ ይችላል፡፡
    ለ. የሰበር መቃወሚያ አመልካቹ በሥር ፍርድ ቤቶች ተከራካሪ የነበረ እና ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የሰበር ክርክሩ ተካፋይ ያልነበረ ሆኖ የሰበር ችሎቱ የግድ የክርክሩ ተሳታፊ ሊያደርገው ሲገባ ይህን ሳያደርግ ውሳኔ የሰጠ ከሆነ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን ወደ ሥር ፍርድ ቤት መመለስ ሳያስፈልገው ክርክሩን ሰምቶ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

**17. ዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይ ስለሚቀርብ አቤቱታ**

1. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ወይም የሰበር ችሎቱ የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ መነሻ የሆነዉ የሥር ፍርድ ቤት የመጨረሻ ዉሳኔ በሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ፣ በሀሰተኛ የምስክርነት ቃል፣ በሙስና ወይም ሌሎች የወንጀል ጠቀስ ተግባርን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ነዉ በሚል በሰበር ችሎት በዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታዉ የቀረበበት የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ ከሰጠ በኃላ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት የተመለከተዉ ፍርድ

ቤት አቤቱታዉን ተቀብሎ እንዲያከራክር የሰበር ችሎቱ በመዝገቡ ላይ ትእዛዝ በመስጠት ሊመራ ይችላል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የዳግመኛ ዳኝነት አቤቱታዉ የቀረበዉ በሰበር ችሎቱ ዉሳኔ ላይ ከሆነ እና ዉሳኔዉ የተሰጠዉ ሙስናን ወይም ሌሎች የወንጀል ተግባርን መሰረት በማድረግ የተሰጠነዉ በሚል እና አቤት ባይ ይህንኑ በማስረጃ አስደግፎ ያቀረበ እንደሆነ የሰበር ችሎቱ የዳግመኛ ዳኝነት አቤቱታዉን ተቀብሎ ጉዳዩ በሌላ የሰበር ችሎት በዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይ ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እንዲቀርብ ያደርጋል።

**18. ባለጉዳዮች ብዙ ሰዎች ሆነው አንዱ ብቻ የሰበር አቤቱታ ሲያቀርብ**

ለሰበር ችሎቱ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ ምክንያት በሆነው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ባለጉዳዮቹ ብዙ ሆነው አንዱ ብቻ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ የሰበር ችሎቱ የሚሰጠው ውሳኔ የሰበር አቤቱታ ባላቀረቡት ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው የተሰጠው ውሳኔ ያላቀረቡትንም ሰዎች የሚጠቅም ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**19. ስለወጪና ኪሳራ**

ወጪና ኪሳራን በተመለከተ የሰበር ችሎቱ ተገቢ ነዉ ብሎ ያመነበትን ሊወስን ወይም የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር የቀረበውን ዝርዝር መርምሮ እና ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ሃሳብ ተቀብሎ የተጣራውን ሂሳብ እንዲያቀርብለት ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**20. ተፈጻሚነት ስላላቸው ሕጎች**

1. የሰበር ጉዳይን በተመለከተ በዚህ አዋጅና መመሪያ ውስጥ በግልጽ ባልተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ እንደየአግባብነታቸው የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ የወንጀለኛ

መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና ሌሎች ሥነ-ሥርዓታዊ ድንጋጌ ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የዳኝነት እና ሌሎች ክፍያዎችን የሚገዛው ሕግ ለሰበር ችሎት ለሚቀርቡ አቤቱታዎችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2. በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም በልምድ የዳበሩ አሰራሮች ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የተሻሩ ናቸው፡፡

**21. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

1. ይህ መመሪያ ከሚያዚያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት አስቀድሞ በሰበር ችሎቱ በመታየት ላይ ያሉት ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ ፍጻሜ ያገኛሉ።

**22. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ በማንኛውም ጊዜ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊሻሻል ይችላል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ 4 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ቴዎድሮስ ምህረት ከበደ**

**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

**ፕሬዚዳንት**

## <u>አባሪ -1-</u>

## <u>የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ፎርም፡</u>

ቀን.........ወር..........ዓመት

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

<u>አዲስ አበባ</u>

አመልካች.................... ማዕረግ፣ሥም፣ የአባት ሥም. የአያት ሥም/ የተቋም ስም

አድራሻ .........

ተጠሪ፡.......................ማዕረግ፣ሥም፣ የአባት ሥም፣ የአያት ሥም፣ የተቋም ስም ]

አድራሻ ..................

**1. <u>መግቢያ፤</u>**

1.1 የሥር ፍ/ቤት/ቶች ወይም የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ወይም የአስተዳደር አካል/ተቋም... በመ.ቁ..... በቀን......የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ /ብይን/ /ትዕዛዝ/ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ለማሳረም በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ፣ 27 እንደዚሁም በሰበር የሥነ-ሥርዓት መመርያ ቁጥር 4 መሰረት የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነዉ።

1.2 የጉዳዩ ግምት/ዓይነት

1.3 ይርጋ/ የጊዜ ገደብ

1.4 የተከራካሪ ወገኖች ችሎታ

1.5 አቤቱታው በአመልካች ወይም በውክልና ስለመቅረቡ

1.6 ስለመጥሪያ አደራረስ መግለጫ

1.7 የውሳኔ/የትዕዛዝ ግልባጭ አባሪ ስለመደረጉ

1.8 በተጨማሪ ጉዳዩች ላይ አባሪ ስለ (አለ)መያያዙ

**2. የሰበር ክርክሩ መነሻ**

*መሰረታዊ ክርክር በተመለከተ ለሚቀርበው አቤቱታ አግባብነት ያለው የስር ፍርድ ቤት ክርክር በአጭሩ መግለጽ፡፡ በዚህ ክፍል ሁሉንም የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ መዘርዘር ሳያስለፈልግ*

*ተፈጽሟል የተባለውን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ለማሳየት የሚረዳዉን ብቻ በአጭሩ መጠቀስ አለበት።*

**3. <u>የሰበር ቅሬታ ነጥቦች/ምክንያቶች፡</u>**

*ተፈጸመ የተባለውን መሰረታዊ የሕግ ክርክር፣ ለክርክሩ መሰረት የሚሆነውን የሕግ ድንጋጌ እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና አንቀጽ 10(1) ከተመለከቱት ውስጥ የትኛው እንደሆነ እና አግባብነቱን እያንዳንዱ ሐሳብ በሐተታ መልክ ሳይሆን በተራ ቁጥር በመስጠት በአጭሩ ለይቶ መግለጽ፡፡*

**4. <u>አመልካቹ (ቾች) ከሰበር ሰሚ ችሎት የሚጠየቅ ዳኝነት፡</u>**

4.1 *አመልካች(ቾች) የሰበር ሰሚ ችሎት እንዲወስንለት የሚጠይቀዉን ዳኝነት በአጭሩ መግለጽ፤*

4.2 *ወጪና ኪሳራ ከጠበቃ አበል ጋር እንዲወሰንለት የሚጠይቅ ከሆነ በቁርጥ ወይም መዝገቡ ውስጥ ባለው ማስረጃ ወይም ዝርዝር የማቅረብ መብት እንዲጠበቅለት የሚፈልግ መሆኑን……ማመልከት አለበት።*

*የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በእዉነት መሆኑን አረጋግጣለሁ።*

*የአመልካች(ቾች) ፊርማ፡*

**አባሪ -2-**

**የሰበር መልስ**

ቀን……ወር……ዓ.ም

የሰ.መ.ቁ………

**ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት**

**ሰበር ሰሚ ችሎት**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

አመልካች………………… [ማዕረግ፣ሥም፣ የአባት ሥም. የአያት ሥም፣ የተቋም ስም ]

አድራሻ ……

ተጠሪ፡……………………[ማዕረግ፣ሥም፣ የአባት ሥም፣ የአያት ሥም፣ የተቋም ስም]

አድራሻ ……

አመልካች በቀን………ጽፈዉ ላቀረቡት የሰበር አቤቱታ ከተጠሪ የቀረበ መልስ የሚከተለዉ ይሆናል።

(በተጨማሪ ጉዳዩች ላይ አባሪ ስለ (አለ)መያያዙ መግለጫ)

1. *የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ*

   *ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዩች የሚነሱ ከሆነ በቅድሚያ መነሳት አለባቸው፡፡*

2. በዋናው ጉዳይ ላይ

   *የሥር ፍ/ቤት/ቶች/የግልግል ዳኝነት/የአስተዳደር አካል……በሰጠዉ ዉሳኔ…..መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ የቀረቡትን የሕ ክርክሮች እና በሰበር ችሎት በተያዘው ጭብጥ ላይ ብቻ ተወስኖ በርዕስ በመለየትና በሰበር ማመልከቻቸው በቀረበው ቅደም ተከተል ለተነሱት ነጥቦች ተራ ቁጥር በመስጠት መልስ ማቅረብ፡፡*

3. *የሚጠየቀውን ዳኝነት መጥቀስ*

የቀረበዉ መልስ በእዉነት መሆኑን መሰረት አረጋግጣለሁ።

የተጠሪ ስምና ፊርማ፡

**አባሪ -3-**

***<u>የሰበር መልስ መልስ ማቅረቢያ ፎርም፡</u>***

ቀን.........ወር..........ዓመት

መ/ቁ--------------------

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

**<u>አዲስ አበባ</u>**

አመልካች...........................ማዕረግ፣ሥም፣ የአባት ሥም. የአያት ሥም/የተቋም ስም

አድራሻ .........

ተጠሪ፡..............................ማዕረግ፣ሥም፣ የአባት ሥም፣ የአያት ሥም/የተቋም ስም

አድራሻ ..................

**የመልስ መልስ**

*በተጠሪ በቀረበዉ መልስ ላይ ብቻ ተወሰኖ የሚብራራ ወይም የሚጠራ ነገር ካለ አዲስ ክርክር ያልተካተተበት የመልስ መልስ ማቅረብ*

የቀረበዉ መልስ በእዉነት መሆኑን መሰረት አረጋግጣለሁ።

የአመልካች ስምና ፊርማ